## ማን ነው የMMR ወይም የኩፍኝ ክትባት መውሰድ የሌለበት?

- ለፀረ-ሕዋሳት/ኣንቲባዮቲክስ neomycin የሚቀጣ ሰውነት ያለው
- ነብሰጡር የሆነች ሴት ወይም ክትባቱን ከወሰዱ በአንድ ወር ውስጥ የማርገዝ እቅድ ያላት ሴት
- ማንም በሽታ ያለበትና በሕክምና መድሃኒት እንደ ኮርቲሶን/cortisone ወይም ፕረደኒሶሎን/prednisolone የሚወስድ እና ለሰውነት በሽታ መከላከል አቅም አሠራር ሊያዳክሙ ስለሚችሉ ይሆናል።
- ማንም ሰው በሃይለኛ ቁስል/ኢንፌክሽን የሚሰቃይ ከሆነ።

## ለበለጠ ማብራሪያ

- ከሃኪምዎ ጋር መወያየት
- በአካባቢዎ የሚገኝ የመንግሥት ጤና ጥበቃ ጽ/ቤትን መጠየቅ
- የእናቶችና ህፃናት ጤና ጥበቃ ክሊኒክ ነርስን መጠየቅ
- የቤተሰብ መምሪያ ክሊኒኮች መረጃ አላቸው
- በቪክቶሪያ መንግሥት የበሽታ መከላከያ ክፍል፥ ስልክ ቁጥር 1300 882 008 ወይም በዌብሳይት፡ www.health.vic.gov.au/immunisation
- ለኩፍኝ ትምህርት ነርስ፥ የዴፍነስ ፋውንዴሽን/Deafness Foundation
  ስልኪ ቁጥር [03] 9887 8683
  ኢሜል፡ rubella@deafness.org.au
  ዌብሳይት፡ www.deafness.org.au

## በቋንቋ የተተረጎሙ

ይህ ጥራዝ ወረቀት በሌሎች የማሕበረሰብ ቋንቋዎች ትርጉም በዴፍነስ ፋውንዴሽን (Deafness Foundation) ጽ/ቤት ይገኛል። የቋንቋ እርዳታ በነፃ ለማግኘት 13 1450 በመደወል የትርጉም አገልግሎት (TIS) ማናገር ይቻላል።

Rubella



Deafness Foundation

*Published by*
*DEAFNESS FOUNDATION (VICTORIA)*
*P.O. Box 42, Nunawading 3131.*
*Telephone (03) 9887 8683 Fax (03) 9887 8848*
*E.mail rubella@deafness.org.au*
*Web site www.deafness.org.au*

*Publication sponsored as a community service by:*

GlaxoSmithKline

*Endorsed by Immunisation Unit, State Government of Victoria*

February 2005
Project CSLV 2100.5.00

*Amharic*

# Rubella

## በማህበረሰቡ ላለ ማንኛውም ሰው ጠቃሚ የእውነታ ጽሁፍ ሲሆን በተለይ ለሴቶች ህፃን በሚወልዱበት እድሜያቸው



በማሕበረሰብ ውስጥ ላሉ ሰዎች ጠቃሚ እውነታዎች

Rubella

## ኩፍኝ (rubella) ምንድን ነው?

ኩፍኝ [እንዲሁም የጀርመን ኩፍኝ ተብሎ ይጠራል] በጣም ኃይለኛና በቫይረስ የሚመጣ/የሚተላለፍ በሽታ ሲሆን በሕፃናት ላይ የተለመደ ይሁን እንጂ ያደጉ ወጣቶችንና አዋቂ ሰዎችንም ሊበክል ይችላል። የበሽታው ምልክት አይታይም ወይም ብዙ ጊዜ እንደተለመደው ትንሽ ትኩሳትን፣ የእጢ እብጠትን፣ የመገጣጠሚያ ሕመምን እንዲሁም በአንገትና በፊት ላይ ሽፍ ያለ ነገርን ከሁለት እስከ ሦስት ቀናት የሚቆይ እንዲወጣ ምክንያት ይሆናል። ሁልጊዜ የመዳን እድሉ የተሟላና ፈጣን ይሆናል።

ሴቶች በመጀመሪያው 20 ሳምታት ፅንስ ላይ በዚህ በሽታ ከተያዙ በጣም አደገኛ ነው። እንዲሁም በሚወለደው ሕፃን ላይ ከባድ ችግር ያመጣል ማለት እንደ ድንቁርና፣ የልብ በሽታና የአእምሮ ጉድለትን ሊያስከትል ይችላል። ይህ ሁኔታ ሲከሰት ኩፍኝ ከተፈጥሮ የመጣ (CRS) ተብሎ ይነገራል።

## ኩፍኝ እንዴት ሊስፋፋ/ሊተላለፍ ይችላል?

እንደ ጉንፋን ኩፍኝም በተመሳሳይ መንገድ ሊተላለፍ ሲችል የታመመ ሰው በሚስልበትና በሚያነጥስበት ጊዜ ሊተላለፍ ይችላል። ብዙ ጊዜ የኩፍኝ ምልክት ለመታየት ሁለት ሳምንታት የሚሆን ሲወስድ ሰዎች በሽታው ከነሱ ጋር ለመኖሩ አያውቁም። በዚህን ጊዜ በሽታውን ለሌሎች ጤነኛ ሰዎች ሊያስተላልፉ ሲችሉ፤ ይህም በመጀመሪያው የእርግዝና ወቅት ላሉ ሴቶች እና ከትባቱን ካልወሰዱ አደገኛ ይሆናል። **ያስተወለደ ጨቅላ በአደጋው ሊጋለጥ የሚችለው በመጀመሪያው እርግዝና ወቅት ይሆናል።**

## ኩፍኝ የሚይዘው ለማን ነው?

ቀደም ሲል በሽታው ያስነበረበት፣ ክትባት ያስወሰደ ሰው ወይም በሆነ ምክንያት የበሽታ መከላከል አቅም የጎደለው ሰው በበሽታው ሊያዝ ይችላል። ብዙ ጊዜ ክትባት በመውሰድ በሽታውን መከላከል ይቻላል ነገር ግን ከ5-10% የበሽታ መከላከያውን የወሰዱ ሰዎች በኩፍኝ ሊያዙ ይችላሉ ምክንያቱም በሰውነታቸው በቂ የበሽታ መከላከያ አቅም ስለማይኖራቸው ይሆናል።

## በተፈጥሮ የሚመጣ ኩፍኝ እንዴት መከላከል እንችላለን?

**የCRS ኩፍኝን መከላከል ይቻላል!** ካልተለመደና ከወሊድ ጋር አብሮ ለሚመጣ ችግር ለመከላከል ሁሉም ሴቶች እርግዝና ከመጀመራቸው በፊት የኩፍኝ በሽታ መከላከያን ለመውሰዳቸው ማረጋገጡ ጥሩ መንገድ ሊሆን ይችላል። የበሽታ መከላከያውን ከወሰዱ በኋላ ለአንድ ወራት የሚሆን አለማርገዝ እንዲሁም ነብሰጡር የሆኑ ሴቶች እስኪወልዱ ድረስ የበሽታ መከላከያ ክትባት መውሰድ የለባቸውም። ህፃናት ሁሉ የበሽታ መከላከያ ክትባት ከወሰዱ በሽታው በማሕበረሰቡ ውስጥ እንዳይዛመት ይጠቅማል።

በአውስትራሊያ ውስጥ ህፃናት ሁለት የተለያዩ መጠን ያለው የMMR (ኀኩፍኝ፣ ጀሮ ደግፍና የጀርመን ኩፍኝ) ክትባት እንዲወስዱ ይደረጋል። አንደኛው ክትባት የሚሰጠው በ12 ወር እድሜ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በ4 ዓመት እድሜ ይሰጣል።

ይህን በማካኄድ ከሶስት በሽታዎች ለመከላከል ይሆናል።

እስከ ወይም በ1966 ዓ.ም የተወለዱ ሰዎች ሁለት ጊዜ የMMR በሽታ መከላከያ ክትባት ለመውሰዳቸው ማረጋገጥ አለባቸው። እነዚህ ሰዎች በቀላሉ ሊታመሙና በሽታውን ወደ ሌሎች ሰዎች የማስተላለፍ ችግር ይፈጥራሉ። እንዲሁም የበሽታ መከላከያ ክትባቱን እንዲወስዱ በማያደፋፈር ራሳቸውንና ህብረተሰቡን ከበሽታው ለመከላከል ይሆናል።

ሴቶች ከማርገዛቸው በፊትና የሰውነት በሽታ መከላከያ አቅም ተመጣጣኝ ለመሆኑ ለማረጋገጥ የኩፍኝ ደም ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል። የሰውነት በሽታ መከላከያ አቅም ዝቅተኛ ከሆነ ወይም ከሌለ የMMR እና የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት በድጋሜ መውሰድ ያስፈልጋል። ከ6 እስከ 8 ወር የመከላከያ ክትባቱን ከተወሰደ በኋላ ተጨማሪ የደም ምርመራ በማድረግ የመጀመሪያው ክትባት መሥራትና አለመሥራቱን ለማረጋገጥ ይሆናል።

## ማን ነው ይበልጡን አደጋ ላይ የሚወድቅ?

በልጅነት ወቅት በተከታታይ የበሽታ መከላከያ ክትባት በማይሰጥበት አገር ለመጡ ሰዎችና እድሜያቸው ከ4 ዓመት እድሜ በታች ወደ አውስትራሊያ ከመጡ የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት ያስፈልጋቸዋል። በተለይ ከኤሲያና አፍሪካ አገር የተወለዱ ሴቶች ከማርገዛቸው በፊት ቀደም መከላከያውን ሲል ስላልወሰዱ የ፫/ኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት እንዲወስዱ ይገደዳሉ።

በልጅነት ወቅት በኩፍኝ በሽታ ቢያዙም በቀጣዩ የሕይወት ዘመን ኩፍኝ አይዝም ለማለት አያስተማምንም። የሰውነት የበሽታ መከላከል አቅም ለመኖሩ ለማረጋገጥ ከእርግዝና በፊት የደም ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል።

## የበሽታ መከላከያ ክትባት የት ነው የሚሰጠው?

በአካባቢዎት ያለው ሐኪም፣ የቤተሰብ መምሪያ ክሊኒክ፣ የማህበረሰብ ጤና ጥበቃ ማእከልና በአካባቢ ባለ የመንግሥት በሽታ መከላከያ አገልግሎት በኩል የMMR/ኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት ማግኘት ይቻላል።

## የሚያስከትለው ችግር- ውስብስብ

በእርግዝና ወቅት የኩፍኝ ክትባት የሚያስከትለው ችግር ከኩፍኝ/ጀሮ ደግፍ/ የጀርመን ኩፍኝ/MMR ክትባት የሚያስከትለው ችግር ጋር ሲወዳደር እምብዛም ለውጥ የለውም። ደሕና አለመሆን፣ መጠነኛ ትኩሳት በግምት ከ6 እስከ 11 ቀናት በኋላ የመከላከያ ክትባቱ እንደተወሰደ በቀዳ ላይ ሽፍታ መታየት የተለመደ ችግር ይሆናል። የመከላከያ ክትባት የወሰዱ ሰዎች ለሌሎች ሰዎች በሽታውን አያስተላልፉም። በክትባቱ ምክንያት የተነሳ በጣም አደገኛ የሆነ ችግር/ውስብስብ ማለት እንደ አእምሮ መናወጥ የመሳሰሉ በጣም ያልተለመዱ ናቸው። ምናልባት ክትባቱን ከወሰዱ ከሚሊዮን ሰዎች አንድ ወይም በታች ቢሆን ነው። የሚያስከትለው ጥቅምና ጉዳቱን ከሃኪምዎ ጋር መወያየት ነው።